# የማሞቂያ ደህንነት

በዊንተር ወራት በእሳት መሞቂያ አጠገብ ተቀምጦ መጽሐፍ ማንበብ ጥሩ ስሜት አለው። ነገር ግን የማሞቂያ መሳሪያዎች በቤት ውስጥ በእሳት ቃጠሎ ምክንያት ለሚከሰቱ ሞቶች ዋነኛ ምክንያቶች መካከል አንዱ እንደሆነ ያውቃሉ? በጥቂት ቀላል የደህንነት መረጃዎች እና ጥንቃቄዎች ፣ አብዛኛው በማሞቂያ ምክኒያት የሚከሰቱ የእሳት አደጋዎችን መከላከል ይችላሉ።

***በዚህ የዊንትር ወቅት ለቅዝቃዜ ሳይጋለጡ ደህንነትዎን ይጠብቁ!***

- እንደ የቤት ማዕከላዊ ማሞቂያ ቦታ (furnace)፣ የእሳት ማሞቂያ(fire place)፣ የእንጨት ምድጃ ወይም ተንቀሳቃሽ ማሞቂያ(portable space heater) የመሳሰሉትን ሊቃጠሉ ከሚችሉ ነገሮች ቢያንስ ሶስት ጫማ ያርቁ።
- ክፍት ከሆኑ የእሳት መሞቂያዎች እና በቤት ማሞቂያዎች ዙሪያ ሶስት ጫማ ያህል የሚርቅ "ልጆች የማይደርሱበት ስፍራ" ይኑርዎት።
- ቤትዎን ለማሞቅ የማብሰያ ምድጃዎን በጭራሽ አይጠቀሙ።
- በአካባቢው ባሉ የመመሪያ ኮዶች እና በአምራቹ መመሪያ መሰረት የማይንቀሳቀሱ የቤት ውስጥ ማሞቂያ መሳሪያዎችን፣ የውሃ ማሞቂያዎችን ወይም ማእከላዊ የማሞቂያ መሳሪያዎችን ብቃት ያለው ባለሙያ እንዲገጥምሎት ያድርጉ።
- ማሞቂያ መሳሪያዎች እና የጭስ ማውጫዎች ብቃት ባለው ባለሙያ በየዓመቱ እንዲጸዱ እና እንዲፈተሹ ያድርጉ።
- ከመኖሪያ ክፍሉ ሲወጡ ወይም ወደ መኝታ ሲሄዱ ተንቀሳቃሽ ማሞቂያዎችን ማጥፋትዎን ያስታውሱ።
- በነዳጅ ለሚሰሩ ማሞቂያዎች ሁልጊዜ በአምራቹ የተገለፀውን ትክክለኛውን ነዳጅ ይጠቀሙ።
- የእሳት መሞቂያው ፍንጣሪዎች ወደ ክፍሉ እንዳይገቡ ለማቆም እንዲቻል ጠንካራ እና የማይነቃነቅ መዝጊያ እንዳለው ያረጋግጡ። አመድን ወደ ብረት መያዣ ውስጥ ከማስገባትዎ በፊት መቀዝቀዝ አለበት። መያዣውን ከቤትዎ ራቅ ያለ ስፍራ ላይ ያስቀምጡ።
- የጭስ አላርሞች መስራታቸውን በየወሩ ይፈተሹ።

***የማሞቂያ መሳሪያዎች አጠቃቀም***

በእንጨት የሚሰሩ ምድጃዎችን የአምራቹን መመሪያዎችን በመከተል ይግጠሙ ወይም በባለሙያ ***ያስገጥሙ***። የካርቦን ሞኖክሳይድ (CO) መመረዝን ለማስወገድ ሁሉም በነዳጅ የሚሰሩ መሳሪያዎች ወደ ውጭ ማስወጫ ሊኖራቸው ይገባል።

በካርቦን ሞኖክሳይድ (CO) የመመረዝ አደጋን ለማስወገድ የካርቦን ሞኖክሳይድ (CO) አላርሞችን ***ይግጠሙ*** እና መስራታቸውን ያረጋግጡ። ከጋዝ የሚሰራ ማሞቂያዎ ውስጥ የሚመጣ ጋዝ ***ከሸተተዎት***፣ እንዳይለኩሱት። ወዲያውኑ የመኖሪያ ቤቱን ለቀው ይውጡ እና በአካባቢዎ ወደሚገኝ የእሳት አደጋ መከላከያ ወይም የጋዝ ካምፓኒ ይደውሉ።

***እውነታ***

ግማሽ የሚሆኑት በቤት ማሞቂያ ምክኒያት የሚነሱ እሳቶች በዲሴምበር፣ በጃንዋሪ እና በፌብሩዋሪ ወራቶች ውስጥ እንደሚከሰቱ ሪፖርት ይደረጋል።

ለነጻ የቤት ደህንነት ፍተሻ ወደ 311 ይደውሉ፣ www.mcfrs.org/mcsafe